# ስለ ፍቅር የታደሙ አዛውንቶች በመቐለ

ሰለሞን ሽፈራው 08-08-17

እንደ አንዳንድ የፍልስፍናው ዓለም ሊቃውንቶች አስተምህሮ ከሆነ መግባባት የሰው ልጆች ተፈጥሯዊ ባህሪ አይደለም፡፡ በአንፃሩ አለመግባባት የሰዎች ተፈጥሯዊ ባህሪ መገለጫ ተደርጎ ሊወሰድ እንደሚችል ነው የዚህ ፍልስፍናዊ እሳቤ አቀንቃኝ ምሁራን አክለው የሚያስረዱት፡፡ ለአብነት ያህልም፤ከዚህ ንድፈ ሃሳባዊ ትንታኔ አኳያ ስለሚነሳው የመከራከሪያ ነጥብ ተገቢነት የማስረዳት ጥረት በማድረግ ረገድ የሚታወቁ አንዳንድ የድህረ-ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጀርመናውያን ፈላስፋዎችን አቋም ማስታወስ ጠቃሚ ይመስለኛል፡፡

ምክንያቱም ደግሞ፤ ለ2ኛው የዓለም ጦርነት መቀስቀስ ዋነኛዋ መንስኤ ቆስቋሽ አውሮፓዊት ሀገር እንደነበረች ከሚነገርላት ጀርመን መገኘታቸው ለጉዳዩ የተለየ ትኩረት ሰጥተው በቂ የጥናትና ምርምር ስራ እንዲሰሩበት ሳያደርጋቸው እንዳልቀረ ይታመናልና ነው እነርሱን በምሳሌነት ማውሳቱ ጠቃሚ የሚሆነው፡፡ እናም ከዚህ አኳያ የሚታወቁት ጀርመናውያን የፍልስፍናው ዓለም ተመራማሪዎች በጥናታዊ ግኝታቸው የደረሱበት ድምዳሜ ‹‹መግባባት ተፈጥሯዊ የሰው ልጆች ባህሪ አይደለም፤ አለመግባባት ግን ተፈጥሯዊ የሰው ልጆች ባህሪ ነው›› የሚል እንደሆነ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ የዚህ ፍልስፍናዊ መሰረተ ሃሳብ አቀንቃኞቹ ጀርመናውያን ልሂቃን የሚያነሱትን የመከራከሪያ ነጥብ፤ በምክንያት አስደግፈው ግልፅ ለማድረግ የሚሞክሩበት ትንታኔም ደግሞ ‹‹አንዱን ማህበረሰብ ከሌላው ማህበረሰብ ጋር፤ ወይም አንዱን ግለሰብ ከሌላ ለእርሱ ፅጉረ ልውጥ መስሎ ከሚታየው ግለሰብ ጋር ተግባብቶ እንዲኖር ለማድረግ የሚቻለው፤ በሁለቱ ግለሰቦች አሊያም ደግሞ ማህበረሰቦች መካከል መፈጠር ያለበትን የጋራ ዕሴት የመፍጠር ስራ በመስራት ሲሆን፤ በአንፃሩ አለመግባባትን ለማስፈን ግን ያን ያህል ብዙ ጥረት የሚጠይቅ ቅድመ ሁኔታ ማሟላት አይጠበቅብንም›› የሚል ነው፡፡

ለዚህም ይመስላል የድህረ-ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጀርመንና ጀርመናውያን ህዝቦች፤ ከየትኛውም ባለፀጋ ሀገር ይልቅ ለመላው ሰብዓዊ ፍጡር ዘለቄታዊ የጋራ ዕጣ ፈንታ መቃናት ይበጃል ተብሎ የሚታመንበትን ፍትሐዊ የመፍትሔ ሃሳብ ደግፈው ሲቆሙ የሚስተዋሉት፡፡ ለማንኛውም ግን የዚህ መጣጥፍ ዋነኛ ዓላማ በቅርቡ መቐለ ከተማ ውስጥ በተካሔደው የአማራና የትግራይ ክልል የሀገር ሽማግሌዎች የምክክር መድረክ ላይ የተገኙ ሁለቱን ወንድማማች ህዝቦች የወከሉ አዛውንቶች ለሁለት ተከታታይ ቀናት መክረው ዘክረው ስላስተላለፉት የጋራ ውሳኔ ጠቀሜታ ጥቂት ተጨማሪ ነጥቦችን ማንሳት ነው፡፡

እንግዲያውስ ለዚህ ሐተታዬ መንደርደሪያ አድርጌ ያቀረብኩት የዘመናችን ዓለም ዓቀፍ ፍልስፍናዊ እሳቤ ላይ የተመለከተውን የመግባባትና አለመግባባት አተረጓጎም ጉዳይ፤ በተለይም ወደእኛ ሀገር ህዝቦች የዕርስ በርስ ግንኙነት መገለጫ ማህበራዊ የጋራ እሴቶች ስናመጣው ምን ማለት እንደሆነ የሚያሳዩ ነጥቦችን እንደሚከተለው ለማንሳት እሞክራለሁ፡፡ ስለዚህም እንደኔ እምነት ከሆነ ‹‹መግባባት ተፈጥሯዊ አይደለም፤ አለመግባባት ነው የሰው ልጅ ተፈጥሯዊ ባህሪ ›› የሚለውን የአውሮፓውያኑ የፍልስፍና ድምዳሜ ወደ ኢትዮጵያ ሀገር አቀፋዊ ተጨባጭ እውነታ አምጥተን ስንተረጉመው፤ ምናልባትም ብዝሃነትን በአግባቡ ስለማስተናገድ አስፈላጊነት ጉዳይ አዘውትረን ከምናነሳው መሠረተ ሃሳብ አኳያ ሲታይ ከፈረንጆቹ ይልቅ እኛ ዘንድ ጠቀሜታው የበዛ መልዕክት አዝሎ እናገኘዋለን ባይ ነኝ፡፡

ይህን የምልበት ዋነኛ ምክንያትም ደግሞ፤ ኢትዮጵያ ማለት ከሰማንያ በላይ የሚሆኑ የየራሳቸው ቋንቋ፤ ባህል፤ ሃይማኖትና ሌላም የብሄራዊ ማንነት መገለጫ ተደርጎ የሚወሰድ ማህበራዊና ስነልቦናዊ ዕሴት ያላቸው ልዩ ልዩ ህዝቦች የሚገኙባት ሀገር ሆና ሳለ፤ ህብረተሰባችን ግን ተፈጥሯዊውን ልዩነት እንደ ፀጋ ከመቁጠር በሚመነጭ ሆደ ሰፊነት፤ እርስ በርስ ተሳስቦ መኖርን ያውቅበታል፡፡ ለአብነት ያህልም ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ የሙብት ጥያቄዎችን ሊያስከትሉ የሚችሉ የጥቅም ቅራኔዎችን እንዴት በጥሞና መክሮ ዘክሮ መፍታት እንደሚቻል የማይገነዘብ አንድም ኢትዮጵያዊ የህብረተሰብ ክፍል የለም ብል ከእውነት መራቅ አይሆንብኝም፡፡ እናም ህብረተሰባችን ከዚሁ የጋራ ግንዛቤው በሚመነጭ የጋራ ጥረት፤ፈርጀ ብዙ አለመግባባቶችን እያረገበና ችግሮቹን እያቃለለ የጋራ ህልውናው መሰረት የሆነችውን እናት ሀገሩን ከተደጋጋሚ የብተና አደጋ ሲታደግ የተስተዋለበት የታሪክ አጋጣሚ ጥቂት አይደለም፡፡  ይህ ሲሆን የሚታይበት መሰረታዊ ምክንያትም፤ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ የህብረተሰብ ክፍል ‹‹መግባባት የሰው ልጆች ተፈጥሯዊ ባህሪ አይደለም፤ አለመግባባት ግን የሰው ልጅ ተፈጥሯዊ ባህሪ ነው›› የሚለውን የጀርመናውያን ፈላስፋዎች እሳቤ በውል የተገነዘበ እስኪመስል ድረስ  የብዝሃነታችን መገለጫ የሆኑት ልዩነቶቻችን የሚጠይቁትን የጥንቃቄ እርምጃ ከመውሰድ ስለማይቦዝን ነው ማለት ይቻላል፡፡

ከዚህ መሠረተ ሃሳብ አኳያ እኛ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች እንደ አንድ ሀገር ህብረተሰብ በርግጥም ይበልጥ ልናዳብረው የሚገባን ጠቃሚ የጋራ ባህል እንዳለን በተሻለ መልኩ የምንገነዘበውም ደግሞ፤ እንደ ሶማልያና ደቡብ ሱዳን ባሉት ጎረቤት ሀገራት ውስጥ የሚስተዋለውን የዕርስ በርስ ትርምስ ከነመንስኤው ማጤን ሲቻል ይመስለኛል፡፡ በተለይም የአንድ ዓይነት ቋንቋ ተናጋሪና እንዲሁም አንድ ዓይነት ባህል የሚንፀባረቅበት ማህበራዊ ስረ መሰረት ያለውና አንድ ሃይማኖት ብቻ የሚከተል ህዝብ የሚኖርባት ጎረቤት ሀገር ሶማልያ በጎሰኝነት አባዜ ምክንያት ለከፋ የብተና አደጋ ስትዳረግ የተስተዋለችበትን የቅርብ ጊዜ አሳዛኝ ታሪክ ግምት ውስጥ አስገብተን ጉዳዩን በቅጡ እንመርምረው ካልን፤ እኛ ኢትዮጵያውያን ህዝቦች ዕርስ በርስ ተሳስቦ ስለመኖር አስፈላጊነት ጠቃሚ የጋራ ባህል እንዳለን መረዳት አይከብድም፡፡

እንደዚህ ዓይነቱ የኢትዮጵያውያን ብሔሮች፤ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የጋራ ማንነት መገለጫ ተደርጎ ሊወሰድ በሚችል መልኩ ከቀደመው የአብሮነት ታሪካችን ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ እጅጉን ጠቃሚ ባህል፤ በየትኛውም የሀገራችን አካባቢ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎችን ሁሉ የሚመለከት ዕርስ በርስ ተሳስቦ የመኖር ዕሴት እንደሆነም ደፍሮ መናገር ይቻላል፡፡ እኔ እንደ አንድ የሰሜን ኢትዮጵያ ተወላጅ የዚች ሀገር ዜጋ ስለጉዳዩ ተጨባጭ እውነታነት የማውቀውን ጥሬ ሀቅ አንስቼ ምስክርነቴን መስጠት ካለብኝ ደግሞ፤ በተለይም የአማራና የትግራይ ብሔር ብሔረሰቦች ጉርብትና የሚገለፅበትን ኢትዮጵያዊ የወንድማማችችነት ስሜት ከማስታወስ የተሻለ አብነት አይኖርም ባይ ነኝ፡፡

ይህን ስል ግን እንዲያው ብቻ አሁን አሁን በሁለቱ የሰሜናዊ ኢትዮጵያ ነዋሪ ወንድማማች ህዝቦች መካከል የሚስተዋለውን ወደ አልተለመደ አሉታዊ ግንኙነት የማምረት አዝማሚያ፤ ለማርገብ ያለመ ‹‹ዋሽቶ የማስታረቅ›› ሙከራ ለማድረግ እየቃጣኝ እንዳይመስላችሁ፡፡ ይልቅስ ሁለቱንም የሰሜን ኢትጵያ ህዝቦች (የአማራና የትግራይ) ዕኩል እንደሚያውቃቸው ግለሰብ ዜጋ፤ ከልጅነት እስከ እውቀት አብሬያቸው ስኖር አሳምሬ የተገነዘብኩትን ስር የሰደደ የአንድነት ስሜት ሳስበው፤ በእርግጥም የኢትዮጵያዊ ወንድማማችነት ምሳሌ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ጥልቀት ያለው ሆኖ ስለሚሰማኝ እንጂ፡፡

ስለዚህም የሁለቱ ወንድማማች ህዝቦች ግንኙነት እጅጉን ዕድሜ ጠገብና ታሪካዊ ገፅታ የተላበሰው ማህበራዊ ስረ መሰረት ባለው ጥልቅ ትስስር የሚገለፅ ተደርጎ እንደተገነባ ለመረዳት የሚቻልባቸው ተጨባጭ እውነታዎች፣ አንዱና

ምናልባትም ዋነኛው ጉዳይ፣ ዕርስ በርስ እየተጋቡ መውለድ መዋለድ ከጀመሩ ዘመናትን ማስቆጠራቸው ነው ማለት ይቻላል፡፡ ስለሆነም የዛሬዋ ኢትዮጵያ ውስጥ እጅግ በርካታ ቁጥር ያላቸውን ከአማራና ከትግራይ ብሔር ተወላጅ እናትና አባት አብራክ የተከፈሉ ዜጎችን ማግኘት እንብዛም የሚያስገርም ጉዳይ አይደለም፡፡ ለዚህም ይመስላል በአንዳንድ የሰሜን ኢትዮጵያ አካባቢዎች ህብረተሰብ ዘንድ፤

የተወለደው ቆባ ፀፀራ፣

በእናቱ ትግሬ ባባቱ አማራ፣

እንደ መይሳው ሞት የማይፈራ…

ወዘተ እየተባለ ሲፎከርና ሲሸለል መስማት የተለመደ ጉዳይ መሆኑ፡፡ ለነገሩማ ከድህረ ዘመነ መሳፍንት ኢትዮጵያ ታላላቅ ነገስታት አንዱ የነበሩት የትግራይ ተወላጁ አፄ ዮሐንስ አራተኛ፣ አንገታቸውን ለደርቡሽ ጂሀዲስቶች ሰይፍ እስከመስጠት የደረሱት ታሪካዊቷን የጎንደር ከተማ ከባእዳውያኑ ወራሪዎች የጥፋት ተልዕኮ ለመታደግ ሲሉ መተማ ዘምተው አይደለምን? እንግዲህ የሁለቱ ህዝቦች ኢትዮጵያዊ ወንድማማች በእርግጥም እድሜ ጠገብ እንደሆነ የሚያረጋግጡ በርካታ የአማርኛና የትግርኛ ስነ ቃሎችን ጨምሮ፣ ሌላ - ሌላም ታሪካዊ ማጣቀሻዎችን እያነሳን ብንነጋገር እጅጉን በጠነከረ ፈረጀ ብዙ ዝምድና የተሳሰሩ እንደሆኑ ነው መረዳት የሚቻለው፡፡ በአጭሩ ሁለቱን የክልል መስተዳድሮች በሚያዋስኗቸው የአማራና የትግራይ አካባቢዎች የሚኖረው ኢትዮጵያዊ አርሶ አደር የህብረተሰብ ክፍል ከብሔር ተወላጅነት ይልቅ የአብሮነቱ ተጨባጭ መገለጫ አድርጎ ለሚወስዳቸው፣ ባህላዊ፣ ማህበራዊና ስነልቦናዊ የጋራ እሴቶቹ ፋይዳ ተገቢ ዋጋ የሚሰጥበት እውነታ እንዳለ ደፍሮ መናገር ይቻላል፡፡

እናም ከዚህ አኳያ እኔን ይበልጥ የሚያስገርመኝ እንቆቅልሽ ጉዳይ ቢኖር፤ አንዳንድ የፌስቡክ ዘመን ፖለቲከኞች ከሚያዛምቱት መርዘኛ ፕሮፖጋንዳ በሚመነጭ ያፈጠጠና ያገጠጠ ጭፍን ጥላቻ ምክንያት፤ የሁለቱን ብሔር ወንድማማችነት ህዝቦች ወዳልተለመደ የጋራ ጥፋት አደጋ ለመውሰድ ሲባል የሚውጠነጠን መሳፍንታዊ ሴራ ተበራክቶ መስተዋሉ ነው፡፡ በተለይም ደግሞ ከጥቂት ዓመታት ወዲህ ይበልጥ እየተባባሰ የመጣ የሚመስለው የዲያስፖራ ተቃዋሚ ፖለቲከኞች ፅንፈኝነት የተጠናወተውን ጭፍን የጥላቻ ስሜት እንደ ‹‹ አዋጭ የትግል ስልት›› የቆጠሩት የሚመስሉ ስልጣን ናፋቂዎቹ የትምክህትና የጠባብ ብሔርተኝነት አስተሳሰብ አቀንቃኝ ቡድኖች፤ ሁለቱን ወንድማማች ህዝቦች ደም ለማቃባት ከመሻት ከሚመነጭ እኩይ ፍላጎታቸው የተነሳ የሚያውጠነጥኑትን መሰሪ ሴራና የሚፈፅሙትን ውስብስብ ደባ ለታዘበ ሰው ጉዳዩ በእርግጥም እንቆቅልሽ ሆኖ እንደሚሰማው ደፍሮ መናገር ይቻላል፡፡

ስለዚህም፤ የእንቆቅልሹን ቋጠሮ በቅጡ መመርመርና መፍታት እንደሚገባ ያመኑ የአማራና የትግራይ ክልል የሀገር ሽማግሌዎች በተለመደው የኢትዮጵያውያን ህዝቦች የጋራ ባህል መከረው ዘከረው መፍትሔ ለማበጀት ሲሉ፤ በቅርቡ መቐለ ላይ ተገናኝተው ነበር፡፡ ስለሆነም በሁለቱ የክልል መስተዳድሮች ውስጥ ከሚገኙ ከእያንዳንዱ ወረዳዎች በነዋሪው ህዝብ ጥቆማ እየተመረጡ እንደተውጣጡ የሚነገርላቸው ታዋቂ የሀገር ሽማግሌዎች ስለፍቅር ለመምከርና ለመዘከር ሲሉ በታደሙበት የመቐለው ሰሞነኛ መድረክ ላይ የተገኙት ከአንድ ሺህ በላይ የሰሜን ኢትዮጵያ አዛውንቶች ለተከታታይ ሁለት ቀናት ያካሔዱት ስብሰባ ምን ይመስል እንደነበር ከሞላ ጎደል የሚያስቃኝ መሰረተ ሃሳብ ነው በዚህ ፅሁፍ ላነሳ የፈለኩት፡፡

እንግዲህ እንደኔ እምነት ከሆነ፤ በአማራና በትግራይ ክልል ወንድማማች ህዝቦች መካካል ያለው ፈርጀ ብዙ ትስስር ምንያህል በጥብቅ የተቆራኘ ታሪካዊ ይዘት ላይ ተመስርቶ እንደተገነባ ለመረዳት ይቻል ዘንድ የመቐለውን ሰሞነኛ የምክክር መድረክ በራሳቸው ተነሳሽነት ያዘጋጁት የሁለቱ ክልሎች የሀገር ሽማግሌ አዛውንቶች፤ የሚያውቁትን ጥሬ ሀቅ እያነሱ ምስክርነታቸውን ሲሰጡ ከተደመጡበት ጥልቅ ማብራሪያ የተሻለ አስረጅ የሚያሻን አይመስለኝም፡፡ ምክንያቱም ደግሞ፤ ያው ሁላችንም በተለያዩ የክልልና የፌደራል መገናኛ ብዙሃን አማካኝነት ተዘግቦ እንደተከታተልነው፤ መቐለ ውስጥ ስለፍቅር የታደሙት ከአንድ ሺ በላይ የሚሆኑ የትግራይና የአማራ ክልል ህዝቦችን ዘመናት ያስቆጠረ ዕርስ በርስ ተሳስቦና ተከባብሮ የመኖር የጋራ ባህል አሳምረው የሚያውቁ የሀገር ሽማግሌዎች፤ ለሁለት ቀናት ትኩረት ሰጥተው የመከሩ የዘከሩባቸው መሰረታዊ ቁምነገሮች፤ብዙ እውነት እንዲገባን ማድረግ የሚችሉ ሆነው አግኝቻቸዋለሁና ነው፡፡ በግልፅ አነጋገር፤ የአማራና የትግራይ ብሔር ህዝቦች ጉርብትና የሚታወቅበት አጠቃላይ እውነታ፣ እጅግ ከጠበቀ ማህበራዊ ትስስር የሚመነጭና አልፎም ለዚህ ሀገር ነፃነት ሲባል አብረው እየዘመቱ በከፈሉት ተደጋጋሚ መስዋዕትነት ጭምር የሚገለፅ መሠረተ ፅኑ አንድነትን ሲገነቡ የቆዩ ስለመሆናቸው ነው እኔ በግሌ ፈቱንም የምረዳው፡፡

ከዚሁ ለዘመናት ሲወርድ ሲዋረድ ከመጣ ታሪካዊ ትስስራቸው እንደሚመነጭ በሚታመንበት የወንድማማችነት ስሜት ምክንያት ለጋራ መብትና ነፃነታቸው መረጋገጥ ሲሉ አብረው ከመታገል ቦዝነው እንደማያውቁም ነው ስለሁለቱ ህዝቦች የአብሮነት ታሪክ የሚያወሱ የፅሁፍ ሰነዶች የመዘገቡት፡፡ ለዘህም ደግሞ የደርግ ኢ.ሰ.ፓ. ወታደራዊ የአፈና አገዛዝ በመላው የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ጫንቃ ላይ ተፈናጦ የሚያናጥርበት የጨለማው ዘመን ያበቃ ዘንድ አበክረው ከታገሉት የሀገራችን ህዝቦች የትግራይና የአማራ ቀዳሚ ስፍራ እንደሚይዙ እኔ ራሴም የዓይን ምስክር ነኝ፡፡

እንዲሁም የአፄ ሃይለ ስላሴ ዘውዳዊ አገዛዝ በመላው የሀገራችን ህዝቦች ላይ ሲፈፅም የኖረውን ፈርጀ ብዙ ጭቆና መቃወም እንደሚቻል ያሳየ የአመፅ እንቅስቃሴ የተጀመረው በትግራይና በአማራ ብሔር አርሶአደሮች እንደነበርም ጭምር የታሪክ ድርሳናት ያመለክታሉ፡፡ ለዚህ ታሪካዊ እወነታ እንደ አብነት የሚጠቀሱት አስረጂዎችም፤ የትግራይ ህዝብ በንጉሱ ፊውዳላዊ ስርዓት ይፈፀምበት የነበረውን ብሔራዊና መደባዊ ጭቆና ተቃውሞ የተነሳበት የቀዳማዊ ወያኔ ንቅናቄና እንዲሁም ደግሞ የአማራ ህዝብ አካል የሆኑት የጉጃም አርሶአደሮች በዚያው ዘመን ተመሳሳይ የእንቢ አልገዛም ባይነት እንቅስቃሴ ያካሄዱበትን ታሪካዊ እውነታ ማስታወስ ይቻላል፡፡ ይልቁንም በቅርብ ጊዜው ኢህአዴግ መራሽ ፀረ ጭቆና የትጥቅ ትግል ሂደት የትግራይና የአማራ ክልል ህዝቦች ከመቸውም በላይ ለጋራ መብትና ጥቅማቸው መረጋገጥ ሲሉ እጅ ለእጅ ተያይዘው ከደርግ አምባገነናዊ የአፈና አገዛዝ ጋር የሞት ሽረት ፍልሚያ ገጥመዋል፤ በዚያው ልክም አብረው እየሞቱ አንድ ጉድጓድ ውስጥ እስከመቀበር ደርሷል፡፡

ታዲያ ከዚያ ሁሉ የፀረ ጭቆና ትግላቸው በሁዋላ የተከፈለው ፈርጀ ብዙ መስዋዕትነት ፍሬ አፍርቶ፤ መላው የሀገራችን ብሔሮች፤ብሔረሰቦችና ህዝቦች ዕርስ በርስ ተፈቃቅደው የመሰረቷት ፌደራላዊት፤ ዴሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ እውን ስትሆን የአማራንና የትግራይን ወንድማማች ህዝቦች የማያግባባ ምን ምክንያት ተፈጠረ ይሆን? ደሞስ እንኳን ከላይ የተመለከተውን ያህል ዘመናትን ያስቆጠረ ጥብቅ ታሪካዊ ትስስር ያቆራኛቸውን የትግራይንና የአማራን ህዝቦች፤ መላውን የዚች ሀገር ብሔር ብሔረሰቦች እርስ በርስ ተፈቃቅደውና ተፈቃቅረው እንዲኖሩ ለማድረግ ያስቻለ ሕገ መንግስታዊ ስርዓት ፈጥረን የለ እንዴ? ወዘተ የሚሉ ጠያቂዎችን እያነሳን በጥልቀት እንድንወያይ የሚጋብዝ ጉዳይ ሆኖ ነው ለኔ የሚሰማኝ፡፡

እናም ጉዳዩን ከዚህ አኳያ እናጢነው ከተባለ፤ በተለይም የትግራይና የአማራ ብሔር ህዝቦች ለማመን የሚያዳግት ፈርጀ ብዙ መስዋዕትነት ከፍለው የተቀዳጁትን የግንቦት 20 ድል ተከትሎ ሀገራችን ውስጥ የተከፈተው አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ገና ከመነሻው ጀምሮ ባልተዋጠላቸው አንዳንድ የወደቀው ስርዓት ርዝራዦች አማካኝነት ሆን ተብሎ የተሸረበ ፖለቲካዊ ሴራ ስለመኖሩ ነው ደፍሮ መናገር የሚቻለው፡፡ ስለሆነም፤ ይህን መሰሉ የግዛት አንድነትን ናፋቂ የተቃውሞው ጎራ ፖለቲከኞች እጅጉን በተጠና መሳፍንታዊ ሴራ ነገር እያወሳሰቡ ሁለቱን ወንድማማች ህዝቦች ለማቃቃርና ብሎም ደም ለማቃባት ሲሞክሩ የሚስተዋሉበት እኩይ እንቅስቃሴ ፈፅሞ ተቀባይነት እንዳይኖረው ማድረግ ይቻል ዘንድ፤ በተለይም የጉዳዩ ባለቤቶች የሆኑትን የአማራና የትግራይ ብሔር ህዝቦች ዕርስ በርስ እየተገናኙ በግልፅ እንዲወያዩ የማድረግ አስፈላጊነት ለነገ ሚባል አይደለም፡፡

ምክንያቱም ደግሞ በቅርቡ በመቐለ ከተማ ስለፍቅር ለመምከር የታደሙት የአማራና የትግራይ ክልል ህዝቦችን የወከሉ ከአንድ ሺህ በላይ ታዋቂ የሀገር ሽማግሌዎች፤ ለሁለት ቀናት ግልፅ ውይይት ካካሄዱበት መድረክ መረዳት እንደሚቻለው ከሆነ፤ ችግር እየፈጠረ ያለው በጥቂት ‹‹ተምረናል›› ባዮች የፖለቲካ ልሂቃን የሚውጠነጠን መሳፍንታዊ የማነካካት ሴራ እንጂ፣ ብዙሐኑን የሁለቱ ብሄሮች ተወላጅ ህብረተሰብ የሚመለከት ጉዳይ አይደለምና ነው፡፡ ስለዚህም፤ አሁን አሁን እየተባባሰ ከመጣው የዲያስፖራ ተቃዋሚ ፖለቲከኞች ፅንፈኛ አቋም እንደሚመነጭ የሚታመንበትን በሀገራችን ብሔሮች፤ ብሔረሰቦችና ህዝቦች መካከል አላስፈላጊ መቃቃርና ግጭት እንዲፈጠር የማድረግ ዓላማ ያለው ጭፍን የጥላቻ ስሜት ተቀባይነት በማሳጣት ረገድ ምትክ የማይገኝለትን ቁልፍ ሚና ሊጫወት የሚችለው ብዙሀኑ የህብረተሰብ ክፍል፤ የአደጋውን አሳሳቢነት በቅጡ ተገንዝቦ ህገመንግስታችን ላይ የተደነገጉ የጋራ ስምምነቶችን መሰረት ባደረገ መልኩ እየተወያዩ ችግሮችን ይፈታ ዘንድ እድል ሊሰጠው ይገባል የሚል ፅኑ እምነት አለኝ፡፡

አለበለዚያ ግን ይህ የዘመነ ፌስቡክ ፈርጀ ብዙ የመረጃ ልውውጥ መረብ የፈጠረላቸውን ምቹ ሁኔታ እንደ መልካም አጋጣሚ ተጠቅመው በሚያቀነባብሩት የበሬ ወለደ አይነት ውዥንብራቸው አማካኝነት፤ አንዱን የብሔር ወይም ደግሞ የብሔረሰብ ህዝብ ከሌላኛው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ጋር ጦር እንዲማዘዝ ለማድረግ ያለመ ሴራ በማውጠንጠን እንቅልፍ አጥተው የሚያድሩት የትምክህትና የጠባብ ብሔርተኝነት ፖለቲካዊ አስተሳሰብ አቀንቃኝ ሃይሎች፣ መቼም ቢሆን እንደማይተኙልን ከእስከዛሬው ተደጋጋሚ ሙከራቸው መረዳት አያዳግትም፡፡ ስለዚህም ለአማራና ለትግራይ ክልል ህዝቦች ብቻም ሳይሆን፣ ለመላው የሀገራችን ብሔር -ብሔረሰቦች ዘለቄታዊ የጋራ እጣ ፋንታ ጭምር የሚበጀው ቀና መንገድ እርስ በርስ ተፈቃቅደንና ተፈቃቅረን የምንኖርባትን ፌደራላዊት፣ ዴሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ ኢትዮጵያን ለመመስረት ስንል መክረን፣ ዘክረን፣ ባፀደቅነው ሕገ መንግስታዊ የቃል ኪዳን ሰነድ ላይ የተደነገጉትን የችግር አፈታት አግባቦች የተከተለ ሰላማዊ መፍትሄ መስጠት በሚቻልበት አማራጭ ሀሳብ ዙሪያ፣ ግልፅ ውይይት ማካሄድና ተነጋግሮ መደማመጥ ብቻ እንደሆነ ሰሞኑን በመቀለ የታደሙት አዛውንቶች ከደረሱበት ማጠቃለያ የተሻለ ማሳያ አያስፈልግም ባይ ነኝ፡፡ ምክንያቱም ደግሞ፣ በሀገራችን ብሔሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች መካከል መሰል ቅሬታ የሚፈጥሩ ክፍተቶችን መድፈን የሚቻለው ሕገ መንግስቱ ያለ አንዳች መሸራረፍ ተግባራዊ ሲደረግ እንደሆነ ይታመናልና ነው፡፡ በተረፈ ግን የሰይጣን እግሩ ይሰበር እያልኩኝ እዚህ ላይ አበቃለሁ፡፡ መዓ ሰላማት!